የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.58
ADDIS ABABA 7th September, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺/፪ሺ፲ ዓ.ም

የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ..........................................ገጽ ፲ሺ፬፻፴፱

## Content

Proclamation No.1090/2018

Hazardous Waste Management and Disposal Control Proclamation.......................--Page 10439

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺/፪ሺ፲

### የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ

የአደገኛ ቆሻሻዎች በሀገራችን ከሚታዩ አካባቢያዊ ችግሮች መካከል ዋነኛ በመሆኑ፣

ከአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ እና አወጋገድ ጉድለት ሣቢያ ተያይዞ በአካባቢ ላይ እየደረሰ ያለውን የብክለት ችግር መከላከልና መቆጣጠር በማስፈለጉ፣

አደገኛ ቆሻሻዎች በአግባቡ ባለመያዛቸው በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ለመከላከልና የአደገኛ ቆሻሻዎች እንቅስቃሴ፣ መመንጨት፣ መጓጓዝ፣ መከማቸት፣ መታከም፣ ለዳግም እና መልሶ ጥቅም መዋል እና ማስወገድ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO.1090/2018

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR HAZARDOUS WASTE MANAGEMENT AND DISPOSAL CONTROL

WHEREAS, hazardous waste are among one of the main environmental problems in our country;

WHEREAS, it is important to prevent and control problems of environmental pollution caused by the mismanagement and disposal of hazardous waste;

WHEREAS, creating a system to control the generation, storage, treatment, recycling and reuse, transportation, disposal and movement of hazardous wastes is of paramount importance to prevent harm to human and animal health as well as the environmental due to the mismanagement of hazardous waste;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 22.65

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

፩/ "የባማኮ ስምምነት" ማለት አደገኛ ቆሻሻዎች ወደ አፍሪካ እንዳይገቡ ለማገድ እና በአፍሪካ አገሮች መካከል የአደገኛ ቆሻሻዎችን ድንበር ዘለል ዝውውር እንዲሁም አወጋገድ ለመቆጣጠር የተደረገውን የባማኮ ስምምነት ነው፤

፪/ "የባዝል ስምምነት" ማለት የአደገኛ ቆሻሻ ድንበር ዘለል እንቅስቃሴ፣ ዝውውርና ማስወገድን ለመቆጣጠር የተደረገው የባዝል ስምምነት ነው፤

፫/ "ማስወገድ" ማለት በዚህ አዋጅ አባሪ ሦስት ላይ የተጠቀሰውን ማንኛውም የአደገኛ ቆሻሻ አወጋገድ የሚያካትት ድርጊት ነው፤

፬/ "አስወጋጅ" ማለት አደገኛ ቆሻሻን በማስወገድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤

፭/ "አካባቢ"ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ-ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሯዊ ሁኔታዎች በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

፮/ "ለአካባቢ ተስማሚ የቆሻሻ አያያዝ" ማለት በአደገኛ ቆሻሻዎች አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የሰው ጤና፣ አካባቢን እና ሀብት ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ሊተገበሩ የሚችሉ ሁሉንም እርምጃዎችን መውሰድ ነው፤

፯/ "ላኪ" ማለት አደገኛ ቆሻሻን ከኢትዮጵያ ወደ

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "hazardous waste management and disposal control Proclamation No. 1090/2018".

**2. Definition**

In this Proclamation:

1/ "Bamako Convention" means the Bamako Convention on the Ban of the Import of hazardous waste into Africa and the Control of Trans-boundary Movement and Management of Hazardous Waste within Africa;

2/ "Basel Convention" means the Basel Convention on the Control of Trans-boundary Movement of Hazardous Waste and their Disposal;

3/ "disposal" means any hazardous waste disposal operation specified in Annex Three of this Proclamation;

4/ "disposer" means any person who engaged in the disposal of hazardous waste;

5/ "environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by humans, their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living beings, including but not restricted to, land, atmosphere, weather and climate, water, living things, sound, odour, taste, social factors, and aesthetics;

6/ "environmentally sound management of wastes" means taking all practicable steps to ensure that hazardous wastes are managed in a manner which shall protect human health and the environment against the adverse effects which may result from such wastes;

7/ "exporter" means any person who exports

፰/ "አመንጪ" ማለት ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን የሚያመነጭ ሰው ሲሆን፣ አመንጪው ባልታወቀበት ሁኔታ አደገኛ ቆሻሻውን በማወቅ ወይም ባለማወቅ በይዞታው ሥር አድርጎ የሚገኘው ሰው ነው፤

፱/ "አደጋ" ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ፣ በብዝሃ ህይወት እና በንብረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የአንድ ነገር አካል ወይም ሁኔታ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው፤

፲/ "አደገኛ ቆሻሻ" ማለት በዚህ አዋጅ በአባሪ አንድ የተዘረዘሩ ቆሻሻዎች ምድብ ውስጥ የሚካተት እና በአባሪ ሁለት የተዘረዘሩ ባህሪያት ያላቸውን ቆሻሻዎች የሚያጠቃልል እና ሚኒስቴሩ በመመሪያ አደገኛ ቆሻሻ በማለት የሚወስናቸውን ማንኛውንም ቆሻሻ ይጨምራል፤

፲፩/ "አስመጪ" ማለት አደገኛ ቆሻሻን ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ ሰው ነው፤

፲፪/ "መለያ" ማለት የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በአደገኛ ቆሻሻ ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎቹ ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ በሚታይ መልኩ የተለጠፈ ወይም ከእነዚሁ ጋር የተያያዘ መግለጫ ነው፤

፲፫/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለዉጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭/ "ብክለት" ማለት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገን ማንኛውም ግዴታ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረ ነገራዊ፣ ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባህርይን በመለወጥ የተፈጠረ፣ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤

፲፮/ "መልሶ መጠቀም" ማለት አንድን አደገኛ

8/ "generator" means any person who generates hazardous wastes or, in case where the generator is not known, a person who knowingly or unknowingly possesses the hazardous wastes;

9/ "hazard" means the inherent characteristics of a substance agent, or situation having the potential to cause adverse effects or damage to human or animal health, the environment, biodiversity and property;

10/ "hazardous waste" means wastes that belong to any category contained in Annex One of this Proclamation, and possessed any of the characteristic contained in Annex Two; including those wastes that might be categorized as hazardous waste by the directive to be issued by the Ministry;

11/ "importer" means any person who import a hazardous waste into Ethiopia;

12/ "label" means a written, printed or graphic matter attached boldly to the immediate container of a hazardous and the outside container or wrapper of the immediate container;

13/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of the Environment, Forest and Climate Change, respectively;

14/ "person" means any natural or juridical person ;

15/ "pollution" means any condition which is hazardous or potentially hazardous to human health, safety, or welfare or to living things created by altering any physical, radioactive, thermal, chemical, biological or other property of any part of the environment in contravention of any obligation, limitation or restriction made under any other relevant law;

16/ "recycle" means converting of hazardous

፲፯/ "መልቀቅ" ማለት በማወቅም ይሁን በቸልተኝነት አንድ አደገኛ ቆሻሻን ወደ አካባቢ ማስወጣት ነው፤

፲፰/ "አግባብነት ያለው ባለስልጣን" ማለት የአካባቢ የደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እና የሚመለከተው የክልል መንግስት ወይም የከተማ አስተዳደር ባለስልጣን ነው፤

፲፱/ "በድጋሚ መጠቀም" ማለት አደገኛ ቆሻሻን ቀድሞ ለተሰራበት ዓላማ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውልበት አሰራር ነው፤

፳/ "ማከማቻ ማዕከል" ማለት አደገኛ ቆሻሻ ለማከማቸት የተለየ ስፍራ ነው፤

፳፩/ "አጓጓዥ" ማለት አደገኛ ቆሻሻዎችን በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፳፪/ "ማከም" ማለት የአደገኛ ቆሻሻዎች ጎጂነትን ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት የሚከናወን ተግባር ነው፤

፳፫/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን አዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ይጨምራል፤

፳፬/ በወንድ ፆታ የተገለፀው ማንኛውም አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. ዓላማ

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት፤

፪/ በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ፣ በብዝሃ ህይወት እና በንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ማስቀረት፡፡

## ፬. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ፦

፩/ በዚህ አዋጅ በአባሪ አንድ የተዘረዘሩ ቆሻሻዎች ምድብ ውስጥ በሚካተቱ ቆሻሻዎች ላይ እና በአባሪ ሁለት የተዘረዘሩ ባህሪያት ያላቸው ቆሻሻዎች ላይ እንዲሁም ሚኒስቴሩ በመመሪያ አደገኛ ቆሻሻ በማለት የሚወስናቸውን ማንኛውንም ቆሻሻዎች ላይ፤

፪/ በመላ ሃገሪቱ የአደገኛ ቆሻሻ በሚያመነጭ፣ በድጋሚ በሚጠቀም፣ መልሶ በጥቅም ላይ በሚያውል፣ በሚያከማች፣ በሚያጓጉዝ ወይም

17/"release" means discharging of hazardous wastes to the environment intentionally or negligently;

18/ "responsible authority" means the Ministry of Environment, Forest and Climate Change and the responsible regional state or city administration authority;

19/"reuse" means an operation of re-using hazardous waste for its original purpose;

20/"storage facility" means a place designated for the storage of hazardous wastes;

21/"transporter" means a person engaged in the transportation of hazardous waste;

22/"treatment" means action taken to reduce or avoid hazardous impact of wastes;

23/"State" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

24/any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Objective

This Proclamation shall have the following objectives:

1/ Create a system for the environmentally sound management and disposal of hazardous Waste

2/ Prevent the damage to the human or animal health, the environment, biodiversity and property due to the mismanagement of hazardous waste.

## 4. Scope of Application

This Proclamation shall apply to any:

1/ waste that belong to any category contained in Annex One of this Proclamation, and waste possesses any of the characteristic contained in Annex Two; as well as on those wastes that might be categorized as hazardous waste by the directive to be issued by the Ministry;

2/ person who generates, reuses, recycles, stores, transports, or disposes hazardous waste at large in nation.

## ምዕራፍ ሁለት
## የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ

**የንጹህ ምርት መርሆዎች**

ማንኛውም የምርት አምራች አደገኛ ቆሻሻን ለመቀነስ የሚከተሉትን የንጹህ ምርት መርሆዎች መከተል አለበት፡

፩/ በአመራረት ሂደት ውስጥ በጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊገኝ የሚችለውን አደገኛ ንጥረ ነገር በመቀነስ ወይም በማስወገድ የአደገኛ ቆሻሻ ልቀትን መቀነስ፣

፪/ የምርት ሂደትን በመቆጣጠር፦

ሀ) የግብዓቱን ወይም የምርቱን ብክነት መቀነስ፤

ለ) የምርቱ የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ እንዲሰበሰብና ለዳግም ጥቅም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ መፍጠር፡፡

**የአደገኛ ቆሻሻ አመንጪ ኃላፊነት**

የአደገኛ ቆሻሻ አመንጪ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፦

፩/ አደገኛ ቆሻሻን የመሰብሰብ፣ የመለየት፣ የማስወገድ ወይም ፈቃድ ባለው አካል እንዲሰበሰብ፣መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲወገድ ማድረግ፤

፪/ አደገኛ ቆሻሻው የተከማቸበት ኮንቴነር በአግባቡ መታሸጉን እንዲሁም በግልፅ ሊታይ በሚችል መልኩ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መለያው መጻፉን ማረጋገጥ፤

፫/ በአደገኛ ቆሻሻ ጊዜያዊ ማከማቻ ማዕከሉ የሚገኙትን የአደገኛ ቆሻሻ ዓይነትና መጠን የተመለከተ መዝገብ መያዝ፣ እና መዝገቡን በተቆጣጣሪ አካል በተጠየቀ ጊዜ የማሳየት፣

፬/ በጊዜያዊ የማከማቻ ሥፍራ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ወር በላይ ያለማከማቸት፡፡

**አደገኛ ቆሻሻ ላይ መለያ ስለማድረግ**

፩/ ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አመንጭ፣ አከማች፣ አጓጓዥ ወይም አስመጭ ለአደገኛ ቆሻሻው ግልጽ የሚታይ መለያ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የአደገኛ ቆሻሻ መለያው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

ሀ) የአመንጪው ሙሉ አድራሻ፣

## PART TWO
## MANAGEMENT OF HAZARDOUS WASTE

5. **Cleaner Production Principles**

Any producer shall adopt the following clean production principles to minimize hazardous waste:

1/ minimize the release of hazardous waste by reducing or eliminating the hazardous substances in the raw materials during the production process;

2/ monitoring the production process by:

a) reducing the wastage in input and product;

b) creating conditions necessary for the collection and reusability or recyclability of the product after its expiry period.

6. **Responsibility of Hazardous Waste Generator**

Hazardous waste generator shall have the following responsibilities:

1/ collect, segregate and dispose or cause to be collected, recycled or disposed of hazardous waste by authorized body;

2/ ensure that the container of hazardous waste are properly packed and conspicuously labeled with Amharic and English languages;

3/ keep record on the type and quantity of hazardous waste that exist at the temporary hazardous waste storage facility; and show the record at any time when requested by inspector;

4/ not to store a hazardous waste at a temporary storage facility for a period exceeding one month.

7. **Labeling of Hazardous Waste**

1/ Any hazardous waste generator, collector, transporter or importer shall conspicuously label the hazardous waste.

2/ The label of hazardous waste shall contain the following information:

a) full address of th...

ሐ) መደበኛ አያያዝ እና የአያያዝ ዘዴ፣

፫/ ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አመንጭ፣ አከማች፣ አጓጓዥ ወይም አስመጭ በቆሻሻው ላይ ወይም መያዣው ላይ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ቋንቋዎች በግልጽ የሚታይ የማስጠንቀቂያ ወይም የማሳሰቢያ ጽሑፍ ወይም ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

## ፰. አደገኛ ቆሻሻን ስለማጓጓዝ

፩/ አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ፈቃድ ጠያቂው ለዚሁ ዓላማ በሚወጣ መመሪያ የተመለከተውን መስፈርት ማሟላቱን ሲያረጋግጥ በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፣ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

፫/ አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፬/ ማንኛውም አደገኛ ቆሻሻ አጓጓዥ ቆሻሻው በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲሁም ቆሻሻ በድጋሚ በጥቅም ላይ ሊውል የመቻል ሁኔታን እና ቀጣይ ማከምን በማያናጋ መንገድ ማጓጓዝ አለበት።

፭/ አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ለአሽከርካሪዎቹ ስለአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና ማጓጓዝ ላይ ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ አለበት፡፡

፮/ አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ተቋም በድንገተኛ ሁኔታ በሚያጋጥም ልቀት በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት ወይም በአካባቢ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ ጉዳቶች የሚመነጭ የኃላፊነት ካሣን ለመክፈል እንዲቻል ለሚጓጓዘው አደገኛ ቆሻሻ በቂ የመድህን ሽፋን የተደረገለት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፯/ አደገኛ ቆሻሻ በማጓጓዝ፣ በማመንጨት፣

c) formal management and methods of management.

3/ Any hazardous waste generator, collector, transporter or importer shall affix conspicuous warning or caution sign or text on the container in Amharic and English language or other languages of the country as may be necessary.

## 8. Transportation of Hazardous Waste

1/ Any person seeking to engage in the transportation of hazardous wastes shall obtain authorization from the Ministry.

2/ Where the applicant fulfills the requirements stipulated in the directives to be issued for this purpose, the Ministry shall issue the authorization within 30 working days; where the applicant fails to fulfill the requirements, he shall, notify in writing within 15 working days, either to submit additional document or the denial of the authorization.

3/ When the applicant is dissatisfied with the decision he may submit his complaint to the Minister within 15 working days.

4/ Any transporter of hazardous waste shall transport the wastes in a manner that does not affect the human and animal health or the environment or reusability and subsequent treatment of the hazardous waste.

5/ Any person engaged in the transportation of hazardous waste shall train his drivers on the transportation and management of hazardous waste.

6/ Any institution engaged in the transportation of hazardous wastes shall ensure that the consignment is adequately insured to cover liability ensuing from any harm to human or animal health or the environment that may result from any accidental release.

7/ Anybody who infect and damage the

ሂደት አካባቢውን፣ ሰውን እና እንስሳትን የበከለና ለጉዳት የዳረገ ማንኛውም አካል የካሳ ክፍያ ይከፍላል፡፡ የካሳ ክፍያ አፈፃፀሙም ከዚህ በፊት በወጣው የብክለት አዋጅ ድንጋጌ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ለዚሁ ዓላማ በወጣው መመሪያ የተመለከተውን መስፈርት በማሟላት ፈቃዱን በየዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

**ከአደገኛ ቆሻሻ ጭነት ጋር የሚያያዙ ሰነዶች**

፩/ አደገኛ ቆሻሻ በሚጓጓዝበት ወቅት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጡ የፍቃድ ሰነዶች በማንኛውም ጊዜ አጓጓዡ ዘንድ መቀመጥ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተጨማሪ መረጃዎችን የሚያሳይ ሰነድ አጓጓዡ መያዝ አለበት፡

ሀ) የሚጓጓዘው ጥቅል የተነሳበት ቀን እና የሚደርስበት ቦታ ስምና ሙሉ አድራሻ፣

ለ) የአደገኛ ቆሻሻ ሳይንሳዊና የተለምዶ ስሞች፣

ሐ) የጥቅሎቹ ቁጥርና ዓይነት እንዲሁም ጠቅላላ መጠን፣

መ) የአደገኛ ቆሻሻ ላኪና ተቀባይ ሙሉ አድራሻ፣

ሠ) በአደጋ ጊዜ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎችን ያካተተ መረጃ፡፡

፫/ አጓጓዡ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሱትን ሰነዶች አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተሰየመ ተቆጣጣሪ ሲጠይቅ በማንኛውም ጊዜ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

**ማጓጓዝ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች**

፩/ አደገኛ ቆሻሻን የሚያጓጉዝ ማንኛውም አሽከርካሪ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፱ የተጠቀሱትን ሰነዶች ከተቀበለ በኋላ የጭነቱን ሰነዶች ከያዙቱ ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ በመጓጓዝ ላይ ያለ አደገኛ ቆሻሻ በጉዞ ወቅት

and reusing, recycling, treating as well as disposing process of hazardous waste, shall pay compensation for damage according to the provisions of pollution proclamation issued.

8/ The authorization issued to any person pursuant to the provision of sub-article (1) of this Article shall be renewed every year up fulfilling the requirements stipulated in the directives issued for this purpose.

9. **Documents Accompanying the Transportation of Hazardous Waste**

1/ Any transporter of hazardous wastes shall be accompanied by a document issued by the Ministry during transportation:

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the transporter shall accompany documents showing the following additional information:

a) name,date and full address of the initial and final destination of the consignment;

b) scientific and common names of the hazardous waste;

c) number and type of packages as well as the total quantity;

d) full addresses of the consignor and consignee;

e) information on safety measures to be taken in case of an accident.

3/ The transporter shall have a duty to show the documents mentioned in sub-article (2) of this Article at any time to the inspector assigned by responsible authority.

10. **Precautionary Measures to be Taken During Transportation**

1/ The driver who transports hazardous wastes, upon receiving the documents specified in Article 9, shall ensure that the consignment complies with the description contained in the documentation.

2/ Any hazardous wastes being transported shall

፫/ ቆሻሻው በሚጓጓዝበት ወቅት አደጋ ሲያጋጥም አሽከርካሪው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፦

ሀ) ተሽከርካሪው የቆመበትና ጭነቱ የፈሰሰበትን አካባቢ መከለል፤

ለ) የአደጋ ጊዜ የእርዳታ ጥሪ ማድረግ፤

ሐ) ስለተፈጠረው አደጋ ወይም ስለ አፈሳሰሱ ለአስጫኙ፣ ለጥቅሉ ተቀባይና አግባብ ላለው ባለሥልጣን ወዲያውኑ ማሳወቅ፡፡

## ፲፩. አደገኛ ቆሻሻ ስለማከማቸት

፩/ አደገኛ ቆሻሻ በማከማቸት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ አደገኛ ቆሻሻ ለማከማቸት የሚቀርበው ማመልከቻ ለውሣኔ ከመቅረቡ በፊት ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፦

ሀ) አደገኛ ቆሻሻውን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚያስችል በቂ መሣሪያዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች በማከማቻ ስፍራ ስለመኖራቸው፤

ለ) በማከማቻ ስፍራ በቂ የሆነ የጥበቃ እና የጤናና የቅድመ ጥንቃቄ ቁሳቁሶች መኖራቸውን፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ፦

ሀ) ፈቃድ ለመስጠት ሌሎች መሟላት ያለባቸውን ሥርዓቶችና ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች ያዘጋጃል፤

ለ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የአደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ስፍራ ዝርዝር መስፈርት ያዘጋጃል፡፡

፬/ አደገኛ ቆሻሻ ለማከማቸት ፈቃድ የጠየቀው ሰው ፈቃዱ ከተሰጠው በኋላ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በሰው፣ በእንስሳት ወይም በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳት ኃላፊነትን ለመሸፈን ኢንሹራንስ መግባት አለበት፡፡

፭/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ጠያቂው ሰው መስፈርቱን ማሟላቱን ሲያረጋግጥ በ፴ የሥራ

3/ In the event of any accident during transportation of waste the driver shall take the following measures:

a) secure the area around the vehicle and the spill;

b) call emergency services;

c) immediately notify to consignor, the consignee, and the responsible authority on the nature of the spill or accident.

## 11. Hazardous Wastes Storage

1/ Any person seeking to engage in the storage of hazardous wastes shall obtain authorization from the Ministry.

2/ Upon receipt of any application to secure authorization, the Ministry shall ensure fulfillment of the following requirements:

a) adequate facilities and other necessary equipments are available for the safe storage of hazardous wastes;

b) availability of adequate security and health and safety equipments.

3/ Without prejudice to the requirements stipulated under sub-article (2) of this Article, the Ministry, as may be necessary:

a) prepare procedures and other pre-requisites for the licensing of hazardous waste storage;

b) issue requirements pertaining to the storage facilities of hazardous wastes in collaboration with the competent authority.

4/ The applicant to obtain authorization for storage of hazardous waste shall, before commencing operation, enter insurance to cover liability for harm to human or animal health or the environment.

5/ Where the applicant fulfills the requirements, the Ministry shall issue the certificate within

የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

፮/ አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየሁለት ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

## ፲፪. በማከማቸት ወቅት ሊወሰዱ የሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ማንኛውም የአደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ማዕከል ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ፡

፩/ ከተፈቀደለት ሰው ውጪ ወደ አደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ማዕከሉ ውስጥ እንዳይገባ መከልከል አለበት፣

፪/ በማከማቻ ማዕከሉ ውስጥ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች መታሸጋቸውን፣ መለያ የተጻፈባቸው እንዲሁም ተለይተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

፫/ በማከማቻው ስፍራ የሚገኙ አደገኛ ቆሻሻዎች ዓይነት፣ ባህሪና መጠን የተመለከተ መረጃ መያዝና በማንኛውም ጊዜ ሲጠየቅ ለተቆጣጣሪው ማሳየት አለበት፣

፬/ ያልታሰበ አደጋን ለመከላከል የሚያስችሉና ለቅድመ ጥንቃቄ የሚረዱ መሣሪያዎች በተገቢው ስፍራ መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

፭/ የአደገኛ ቆሻሻን ያልታሰበ ልቀት ለመቆጣጠር የዕለት ተዕለት ቁጥጥር በባለሙያ እንዲካሄድ ማድረግ አለበት፣

፮/ የአደገኛ ቆሻሻ ማከማቻ ሥፍራውን ወሰን የሚያሳይ ምልክት ማድረግ አለበት፣

፯/ በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞቹ በመስኩ ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ፲፫. አደገኛ ቆሻሻዎችን በድጋሚ ጥቅም ላይ ስለማዋል

አደገኛ ቆሻሻዎች በሰው እና በእንስሳት ጤናና በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው ተፈትሾ ሲረጋገጥ በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

submit additional document or denial of the authorization.

6/ When the applicant is dissatisfied with the decision he may submit his complaint to the Minister within 15 working days.

7/ The authorization issued to any person pursuant to the provision of sub-article (1) of this Article shall be renewed every two years up fulfilling the requirements.

## 12. Precautionary Measures During Storage

Any owner or administrator of a storage facility shall:

1/ prevent the storage facility against unauthorised access;

2/ ensure that all hazardous wastes stored on the premises are packed, labeled and segregated;

3/ maintain data on the type, character and amount of any hazardous waste stored in the premise and ensure that the data are readily accessible to the inspectors;

4/ ensure that emergency equipments are readily available to contain an accidents;

5/ conduct daily inspection of the hazardous wastes stored on the premises by trained personnel to control the accidental release;

6/ place an indicator to the boundary of hazardous waste storage facility;

7/ ensure that the employees engaged in hazardous waste management has obtained appropriate training in the field.

## 13. Reuse of Hazardous Wastes

Hazardous wastes may be reused where it is proved that it does not cause harm to the human and animal health and environment.

**፲፬. አደገኛ ቆሻሻዎችን ማከምና መልሶ ጥቅም ላይ ስለማዋል**

፩/ አደገኛ ቆሻሻን ለማከምና መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ፈቃድ ይሰጠዋል፡-

ሀ) ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰናቸውን የምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላቱ፣

ለ) ለማከም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ማዕከሉና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል አሰራሩ ሚኒስቴሩ ያዘጋጃቸውን መስፈርቶች ያሟሉ መሆናቸው፣ እና

ሐ) በማከም ወይም መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ማስወገድ የሚችል ሥርዓት ያዘጋጀ መሆኑ፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ፈቃድ ጠያቂው ሰው መስፈርቱን ማሟላቱን ሲያረጋግጥ በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፣ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

፬/ አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈርቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየሁለት ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

**፲፭. አደገኛ ቆሻሻዎችን መልሶ በጥቅም ላይ ከማዋል እና ከማስወገድ በፊት የሚከናወን ህክምና እና አያያዝ**

፩/ አደገኛ ቆሻሻ በሚከማችበት ወቅት በአያያዝ ጉድለት ሳቢያ ሊደርስ የሚችል የዕቃ መሰበርን እና ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ቁሶች መለቀቅ ሥጋትን ለማስቀረት ተገቢ የሆኑ የጥንቃቄ

**14. Treating and Recycling of Hazardous Wastes**

1/ Any person seeking to engage in the treating and recycling of hazardous wastes shall apply to the Ministry and obtain authorization.

2/ Any person submitted application to the Ministry pursuant to sub-article (1) of this Article shall be granted authorization when the fulfillment of the following pre-conditions are verified:

a) complies with the requirements of registration set in the directives of the Ministry;

b) that the recycling facility and its processes are acquiescent in accordance with the requirements set by the Ministry; and

c) put in place a process that disposes the hazardous wastes generated during the treating or recycling process in an environmentally sound manner.

3/ Where the applicant fulfills the requirements, the Ministry shall issue the authorization within 30 working days; where the applicant fails to fulfill the requirements, he shall, within 15 working days, be notified in writing either to submit additional document or denial of the authorization.

4/ When the applicant is dissatisfied with the decision, he may submit his complaint to the Minister within 15 working days.

5/ The authorization issued to any person pursuant to the provision of sub-article (1) of this Article shall be renewed every two years up fulfilling the requirements.

**15. Treatment and Handling before Recycling and Disposal of Hazardous Wastes**

1/ During storage of hazardous waste, appropriate measures shall be taken to prevent the risks of breakage and potential exposure of substances of concern from

፪/ በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከላት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀነስ እና ለማስቀረት አደገኛ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞቹ በመስኩ ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ እና ማስወገጃ ማዕከላት ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች የሥራ ላይ ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢው ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው፡፡

፬/ አደገኛ ቆሻሻን በማከም ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የሚያክመውን የቆሻሻ ዓይነት፣ መጠንና የህክምና ዘዴውን ለሚኒስትሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

፲፮. <u>የአደገኛ ቆሻሻ አወጋገድ</u>

፩/ አደገኛ ቆሻሻ ህክምና ከተደረገለት በኋላ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የማይቻል መሆኑ ከተረጋገጠ መወገድ አለበት፡፡

፪/ አደገኛ ቆሻሻ የማስወገድ ተግባር በዚህ አዋጅ አባሪ ፫ በተዘረዘሩት አማራጮች መሠረት መከናወን አለበት፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ</u>

፲፯. <u>ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ</u>

፩/ ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ፈቃድ ጠያቂው ሰው ለዚሁ ዓላማ በወጣው መመሪያ የተመለከተውን መስፈርት ማሟላቱን ሲያረጋግጥ በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ይሰጣል፣ አመልካቹ መስፈርቶቹን ያላሟላ እንደሆነ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ እንደሚችል ወይም ፈቃዱ የማይሰጥ ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

፫ አመልካቹ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ To prevent or minimize potential risks, the recycling facility shall ensure that employees engaged in hazardous waste recycling duty has obtained appropriate training in the field.

3/ Appropriate safety materials have to be fulfilled to ensure prevention of recycling and disposal facility employees.

4/ Any person who engaged in the treatment of hazardous waste must inform to the Minister, the type, quantity and way of treatment of hazardous waste.

16. <u>Disposal of Hazardous Wastes</u>

1/ The hazardous wastes must be discharged, if it proved recycling of the waste is impossible even after treatment

2/ Hazardous waste disposal activity shall be carried out according to Annex 3 description of this proclamation

## <u>PART THREE</u>

## <u>TRANSBOUNDARY MOVEMENT OF HAZARDOUS WASTES</u>

17. <u>Trans-Boundary Movement of Hazardous Wastes</u>

1/ Any person seeking to engage in the trans-boundary transaction of hazardous wastes shall apply to the Ministry and obtain authorization.

2/ Where the applicant fulfills the requirements prescribed in the directives of the Ministry, the Ministry shall issue authorization within 30 working days; where the applicant fails to fulfill the requirements, he shall, within 15 working days, be notified in writing either to submit additional document or denial of the authorization.

3/ When the applicant is dissatisfied with the decision he may submit his complaint to the Minister within 15 working days.

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አደገኛ ቆሻሻ ተለይቶ ለታወቀ ዓላማ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚፈቅድ መመሪያ ሚኒስቴሩ ያወጣል።

፮/ ከሀገር የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች በባዝል ወይም በባማኮ ስምምነት መሰረት በቅድሚያ የሚጓጓዙበት ሀገር ይሁንታ መገኘቱን ሚኒስቴሩ ማረጋገጥ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው መስፈቶችን በማሟላት ፍቃዱን በየዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡

## ፲፰. ሕገወጥ የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት የአደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ ሕገወጥ ነው የሚባለው፡-

ሀ) ከሚኒስቴሩ የተሰጠ ፈቃድ የሌለው እንደሆነ፣

ለ) ከሚኒስቴሩ የተገኘው ፈቃድ በማጭበርበር ፣የሀሰት መረጃ በማቅረብ ከሆነ፣ እንዲሁም አደገኛ ቆሻሻውን በተገቢው መንገድ የማይገልፅ እንደሆነ፣

ሐ) በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ከተሰጠው መዘርዝር ጋር የማይዛመድ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ) የባዝል ስምምነትን፣ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ማናቸውንም የሀገራችን የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ የሚመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎች የጣሰ እንደሆነ፣

፪/ አደገኛ ቆሻሻ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ እንደሆነ፣ ቆሻሻውን ወደሀገር ውስጥ ያስገባው ሰው በራሱ ወጪ ቆሻሻው ወደ ሀገር ውስጥ በገባ በ፺ ቀናት ውስጥ ወደ መጣበት እንዲመለስ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመተባበር በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገውን ተከታትሎ ያስፈጽማል።

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፱.በክልሎች መካከል የሚደረግ የአደገኛ ቆሻሻ ዝውውር

፩/ እያንዳንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል በመላክ

5/ Without prejudice to the provision of sub-article (4) of this Article, the Ministry shall issue Directive for importation of hazardous waste only for identified purpose.

6/ The Ministry shall ensure that the exportation of hazardous wastes from Ethiopia is in accordance with prior informed consent as stated in the Basel or Bamako conventions.

7/ The authorization issued to any person pursuant to the provision of sub-article (1) of this Article shall be renewed every year up fulfilling the requirements.

## 18. Illegal Transaction of Hazardous Waste

1/ In accordance with this Proclamation, the transaction of hazardous waste deemed to be illegal if:

a) the transaction is conducted without authorization of the Ministry;

b) the authorization has been obtained through fraud, presenting false document, or misrepresents the hazardous waste; or

c) the transaction does not comply to the details provided in the movement documents; or

d) contravenes the Basel Convention, international agreements ratified by Ethiopia, or other national laws relating to hazardous waste transaction.

2/ In the case of illegal import of the hazardous wastes, the importer shall re-export the hazardous waste at his own cost within ninety days from the date of its arrival.

3/ The Ministry, in collaboration with appropriate government organs, shall follow up and implement the provision of sub-article (2) of this Article.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 19. Inter-State Movement of Hazardous Wastes

1/ Each Regional State shall minimize shipment and disposal of hazardous waste to other

፪/ በሀገር ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ክልል ተሻጋሪ አደገኛ ቆሻሻ ለማጓጓዝ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊያገኝ የሚችለው ከቆሻሻው መድረሻ ክልል የአካባቢ ጥበቃ አግባብነት ካለው ተቋም በዝውውሩ መስማማቱን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ አደገኛ ቆሻሻን ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በመውሰድ ማስወገድ የሚቻለው ተረካቢው ክልል ቆሻሻውን መልሶ ለመጠቀም ወይም አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ አቅም እንዳለው እና ፈቃደኝነቱን ለላኪው በጽሁፍ ሲያሳውቅ ብቻ ነው፡፡

**፳. ፍቃድን የማገድና የመሰረዝ ስልጣን**

፩/ ሚኒስቴሩ በማንኛውም ጊዜ አደገኛ ቆሻሻ ለማጓጓዝ፣ ለማከማቸት፣ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ወይም አደገኛ ቆሻሻ ድንበር ዘለል እንቅስቃሴ ላይ ለመሰማራት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ቅድመ ሁኔታዎች ወይም መስፈርቶችን አጓድሎ ሲገኝ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም መስፈርቶችን እስኪያሟላ ድረስ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃዱ የታገደበት ሰው በጊዜ ገደቡ ውስጥ በጉድለት የታየውን ቅድመ ሁኔታ ወይም መስፈርት ሳያሟላ የሚቀር ከሆነ ሚኒስቴሩ ፈቃዱን ሊሰርዝ ወይም እንቅስቃሴውን ወዲያውኑ እንዲያቆም ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በእገዳውና በስረዛው ወቅት አደገኛ ቆሻሻውን በአግባቡ መያዝ አለበት።

**፳፩. ቅጣት**

በወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፡-

፩/ ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ አደገኛ ቆሻሻን ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ እንደሆነ ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ፭፻ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

2/ The Ministry may authorize any inter-state transportation of hazardous waste when the responsible Regional Environmental Protection Authority in the destination Regional State has agreed on the transfer of the waste in writing.

3/ Hazardous waste may be transported from one regional state or urban administration to another regional state or urban administration only if the recipient Regional State or Urban Administration has notified its consent to the sender in writing of its capacity to recycle or dispose of the waste in an environmentally sound manner.

**20. Power to Suspend or Cancel an Authorization**

1/ The Ministry may suspend authorization of any person until realization of preconditions and requirements within 15 working days where the authorized person fails to comply with requirements and conditions of transportation, storage, recycling facility and its processes or trans-boundary movement of hazardous wastes or violates any provision of this Proclamation.

2/ The Ministry may cancel the authorization or order immediate termination of authorization; if the person whose authorization is suspended pursuant to sub-article (1) of this Article fails to rectify the requirements and conditions within the suspension period.

3/ Any person whose authorization has been suspended or canceled has the responsibility to manage the hazardous wastes properly.

**21. Penalty**

Unless it requires higher penalty under Criminal law, Whosoever:-

1/ imports hazardous waste without the authorization of the Ministry shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding five years, and with a fine not less than 500,000 Birr;

፪/ ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን አደገኛ ቆሻሻ በ፺ ቀናት ውስጥ ወደ መጣበት ሀገር ያልመለሰ ወይም ያላስወገደ እንደሆነ ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ፭፻ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፫/ በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው አደገኛ ቆሻሻ አካባቢን የበከለ እንደሆነ ከ፲ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአምስት ሚሊዮን ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፬/ በሕገ-ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ ያስገባው አደገኛ ቆሻሻ አካባቢን የበከለ ሆኖ የተበከለውን አካባቢ ያላከመ እንደሆነ ከ፳ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ፲ሚሊዮን ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፭/ ያለሚኒስቴሩ ፈቃድ፣ ባልታደሰ ፈቃድ አደገኛ ቆሻሻ ያጓጓዘ፣ ያከማቸ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ፭፻ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፮/ ያልታከመ አደገኛ ቆሻሻ ወደ አካባቢው የለቀቀ እንደሆነ የተበከለውን አካባቢ የማከም ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፭ ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት እና ከ፭፻ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፯/ የሀሰት መረጃ በማቅረብም ሆነ በሌላ ማንኛውም መልኩ የተቆጣጣሪውን ሥራ ያደናቀፈ እንደሆነ ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ፶ሺ ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት አደገኛ ቆሻሻ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይህ አዋጅ በሚያዝዘው መሠረት ቅድመ ሁኔታዎችንና መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

**. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ

2/ fails to re-export the hazardous waste imported without the authorization of the Ministry within 90 days shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding five years, and with fine not less than 500,000 Birr;

3/ pollutes the environment by illegally importing hazardous waste shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding ten years, and with fine not less than Five Million Birr;

4/ pollutes the environment by illegally importing hazardous waste, and fails to rehabilitate the environment shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding 20 years, and with a fine not less than Ten Million Birr;

5/ transports, stores or recycles hazardous waste without obtaining authorization from the Ministry and unrenewed authorization shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding five years, and with a fine not less than 500,000 Birr;

6/ discharges or dispose of a hazardous waste into the environment without treating shall, without prejudice to his obligation to treat the environment, be punished with rigorous imprisonment not less than five years and with a fine not less than 500,000 Birr;

7/ provides incorrect information or in any other way impedes the activities of inspector shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding five years and with a fine of not less than 50,000 Birr.

**22. Transitory Provisions**

Any person who has been engaged in the transaction of hazardous wastes before the coming into force of this Proclamation, shall comply with the preconditions and requirements provided in this Proclamation within six month from the date of coming into force of this Proclamation.

**23. Power to Issue Regulations and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣውን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ The Ministry may issue Directive for the proper implementation of the provisions this Proclamation and Regulation issued under sub-article (1) of this Article.

24. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa, this 7th day of September, 2018**

**MULATU TESHOME (D.r)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## አባሪ 1

## ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ የቆሻሻ ምድቦች

### የቆሻሻ ዓይነቶች

- ከሆስፒታሎች ከጤና ጣቢያዎችና ከክሊኒኮች እና ከሌሎች ተቋሞች የሚወገዱ ቆሻሻዎች
- ከመድሀኒቶች አመራረትና አዘገጃጀት የሚወገዱ ቆሻሻዎች
- ተወጋጅ መድሀኒቶች
- ከባዮሳይድስና(ተባይ ማጥፊያ፡ ፀረ ተባይ) ከፋይቶ (ከዕፅዋት)ፋርማሶቲካልስ ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ለእንጨት ማቆያነት ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ኦርጋኒክ አሟሚዎች
- የሣያናይድ ከሚካሎችን የያዙና ለሙቀት እንዲሁም ለቴምፐሪንግ (የሙቀትና የማቀዝቀ ክንዋኔዎች የሚዉሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ጥቅም ላይ ሊዉሉ የማይችሉ ተወጋጅ ይተፈጥሮ ነዳጅ ዘይቶች
- ተወጋጅ ዘይቶች/ዉሃ የሃይድሮካረቦን/ዉሃ ድብልቆች፡ emulsions(ጉሽት)
- ፖሊክሎሪነትድባዩፊናየልስ (ፒሲቢ) እና/ወየንም ፖሊክሎሪነትድትቴረፊናየልስ (ፒሲቲ) ይ ወይንም የተበከሉ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከነዳጅ ማጣሪያና እንዲሁም ከማናቸዉም በከፍተኛ ሙቀት ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎች የሚ ተወጋጅ ካትራሜ
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ቀለሞች ማቅለሚያዎች ፒግመንቶች ላከሮ ቫረኒሽ የሚገኙ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ ሬዚኖች ፕላስቲሳይዘሮች፣ ማጣበቂያ የሚገኙ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከምርምር እና ከማስተማር ተግባራት ጋር የተያያዙና ምንነታቸዉ ያልታወቀ እና/ወየንም አዲ ኬሚካሎች ሆነዉ በሰዉና/ወይንም በአካባቢ ላይ ያላቸዉ ተጽዕኖ ያልታወቀ
- የፈንጂነት ጠባይ ያላቸዉና በሌላ የህግ ማዕቀፍ ያልተካተቱ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከሚመረቱ ከሚቀመሙና አገልግሎት ላይ ከሚዉሉ የፎቶግራፍ ኬሚካሎችና የማቀናበሪያ ቁሳቁ የሚገኙ ተወጋጅ ቆሻሻዎች
- ከብረታብረቶችና ከፕላስቲኮች የገጽታ ስራዎች(surface treatment) ጋር የተያያዙ የኢንዱስ ቆሻሻዎች አወጋገድ
- የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች የአወጋገድ ስራዎች ጋር የተያያዙ የሚከተሉትን ንጥረ ነገሮች የያዙ ቆሻሻዎች

# ANNEX I

## CATEGORIES OF WASTES TO BE CONTROLLED

Waste Streams

- wastes from medical care in hospitals, medical centers and clinics other institutions
- Wastes from the production and preparation of pharmaceutical products
- Waste pharmaceuticals, drugs and medicines
- Wastes from the production, formulation and use of biocides and phytopharmaceuticals
- Wastes from the manufacture, formulation and use of wood preserving chemicals
- Wastes from the production, formulation and use of organic solvents
- Wastes from heat treatment and tempering operations containing cyanides
- Waste mineral oils unfit for their originally intended use
- Waste oils/water, hydrocarbons/water mixtures, emulsions
- Waste substances and articles containing or contaminated with polychlorinated biphenyls (PC and/or polychlorinated terphenyls (PCTs) and/or polybrominated biphenyls (PBBs)
- Waste tarry residues arising from refining, distillation and any pyrolytic treatment
- Wastes from production, formulation and use of inks, dyes,pigments, paints, lacquers, varnish
- Wastes from production, formulation and use of resins, latex, plasticizers, glues/adhesives
- Waste chemical substances arising from research and development or teaching activities which not identified and/or are new and whose effects on man and/or the environment are not known
- Wastes of an explosive nature not subject to other legislation
- Wastes from production, formulation and use of photographic chemicals and processing materi
- Wastes resulting from surface treatment of metals and plastics
- Residues arising from industrial waste disposal operations

- ሜታል ካርቦናይሎች
- ቤሪሊየም፣ የቤሪሊየም ዉህዶች
- የክሮሚየም (VI) ዉህዶች
- የመዳብ ዉህዶች
- የዚንክ ዉህዶች
- አርዜኒክ፣ የአርዜኒክ ዉህዶች
- ሴሌንየም፣ የሴሌንየም ዉህዶች
- ካድሚየም፣ የካድሚየም ዉህዶች
- አንቲሞኒ፣ የአንቲሞኒ ዉህዶች
- ቴሉሪየም፣ የቴሉሪየም ዉህዶች
- ሜርኩሪ፣ የሜርኩሪ ዉህዶች
- ታሊየም፣ የታሊየም ዉህዶች
- እርሳስ፣ የእርሳስ ዉህዶች
- የኢነኦርጋኒክ ፍሉዎሪን ዉህዶች (ከካለሺየም ፍሉዎራይድ በስተቀር)
- ኢንኦርጋኒክ ሣያናይዶች
- አሲዳዊ ሙመት ወይንም ጥጥር አሲድ
- ቤዛማ (ቤዚክ)ሙመት ወይንም ጥጥር ቤዝ
- አስቤስቶስ (አቧራና አሰር (ፋይበር)
- አርጋኒክ የድኝ ዉህዶች
- ኦርጋኒክ ሣያናይዶች
- ፊኖሎች የፊኖል ዉህዶች ከክሎሮ ፊኖል ጭምር
- ኦርጋኒክ አሟሚዎች ከሃሎጅኔትድ አሟሚዎች በስተቀር
- ማናቸዉም የፖሊክሎሪኔትድዳይቤንዞ-ፉራን ተዛማች ኬሚካሎች
- ማናቸዉም የፖሊክሎሪኔትድዳይቤንዞ-ፓራ ዳይኦክሲን ኬሚካሎች
- በዚህ አባሪ ያልተጠቀሱ የኦረጋኖሃሎጅን ዉህዶች

**Wastes having as constituents**

- Metal Carbonyls
- Beryllium; beryllium compounds
- Hexavalent chromium compounds
- Copper compounds
- Zinc compounds
- Arsenic; arsenic compounds
- Selenium; selenium compounds
- Cadmium; cadmium compounds
- Antimony; antimony compounds
- Tellurium; tellurium compounds
- Mercury; mercury compounds
- Thallium; thallium compounds
- Lead; lead compounds
- Inorganic fluorine compounds excluding calcium fluoride
- Inorganic cyanides
- Acidic solutions or acids in solid form
- Basic solutions or bases in solid form
- Asbestos (dust and fibres)
- Organic phosphorus compounds
- Organic cyanides
- Phenols; phenol compounds including chlorophenols
- Ethers
- Halogenated organic solvents
- Organic solvents excluding halogenated solvents
- Any congenor of polychlorinated dibenzo-furan
- Any congenor of polychlorinated dibenzo-p-dioxin

## አባሪ ll

## የአደገኛ ቆሻሻዎች ባሕሪይ

- ፈንጂዎች

ፈነጂ ወይንም የሚወገድ ቆሻሻ ጠጣር ወይንም ፈሳሽ የሆነ ቆሻሻ ( ወይንም የቆሻሻ ውሁድ )፣ በራሱ ሀይል ኬሚካዊ ሪአክሽን በማካሄድ በከፍተኛ ሙቀት ግፊትና ፍጥነት ጋዝ በመፍጠር አካባቢን ለጉዳት የሚዳርግ ማለት ነዉ::

- ተቀጣጣይ ፈሳሾች

"Flammable" የሚለዉ ቃል "inflammable" ከሚለዉ ቃል ጋር ትርጉሙ አንድ ነዉ:: ተቀጣጣይ ፈሳሾች ፈሳሽ ወይንም ፈሳሽ ዉህዶች ወይንም ጥጥር ነገሮችን በሙሙት (በሶሉሽን) ወይንም ሰስፔንሽን የያዙ (ለምሳሌ ቀለሞች፣ ቫርኒሾች ላከሮች ወዘተ. ነገር ግን በአደገኛነት ባህሪያቸዉ ምክንያት በሌላ ምድብ የተፈረጁትን የማያጠቃልሉ)የሙቀቱ መጠን ከ 60.5 °C ያልበለጠ (open-cup test) ወይንም ከ65.6 °C ያልበለጠ (closed-cup tests) ሲሆን ተቀጣጣይ ላቦት (vapour) የሚያመነጩ ናቸዉ:: (የ open-cup tests ሆነ የ closed-cup tests ዉጤቶች በቀጥታ ማነፃፀርም ሆነ በአንድ አይነት መንገድ ተሠርተዉ የሚገኙትም ዉጤቶች አብዛኛዉን ጊዜ ስለሚለያዩ ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርት የማያሟሉትንም በዚህ ትርጓሜ ማካተት የግድ ይላል)::

- ተቃጣይ ጥጥር

ጥጥር ነገሮች ወይንም ጥጥር ቆሻሻዎች በፈነጂነት ከተመደቡት ዉጭ ሆነዉ በመጓጓዝ ላይ በሚያጋጥሙ ሁኔታዎች በቀላሉ ተቃጣይ ወይንም ብፍትጊያ እሳት ልማስነሳት የሚችሉ ወይንም አስተዋፅዎ የሚያደርጉ

- ብግብታዊነት ተቃጣይ ሊሆኑ ይሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች

በመጓጓዝ ላይ በሚያጋጥሙ ምድብ ሁኔታዎች ወይንም ከከባቢ አየር ጋር ግንኙነት ሲፈጠር ብግብታዊነት ሙቀት የሚፈጥሩና እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች

- ከዉሃ ጋር ግንኙነት ሲፈጠር ተቃጣይ ጋዞችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ከዉሃ ጋር ግንኙነት ሲፈጠር ብግብታዊነት ተቃጣይ ሊሆኑ የሚችሉ ወይንም በአደገኛ መጠን ተቃጣይ ጋዞችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች

- ወከሳጅ (ኦክሲዳይዚንግ)

ምንም እንኳን በራሳቸዉ ተቃጣይ ባይሆኑም ኦክሲጂን በመልቀቅ በሌሎች ቁሳቁሶች ላይ እሳት ልማስነሳት የሚችሉ ወይንም አስተዋፅዎ የሚያደርጉ

  - ኦርጋኒክ ፐርኦክሳይድስ

## ANNEX II

## LIST OF HAZARDOUS CHARACTERISTICS

- Explosives

An explosive substance or waste is a solid or liquid substance or waste (or mixture of substances or waste which is in itself capable by chemical reaction of producing gas at such a temperature and pressure and such a speed as to cause damage to the surroundings.

- Flammable liquids

The word "flammable" has the same meaning as "inflammable". Flammable liquids are liquids, or mixtures liquids, or liquids containing solids in solution or suspension (for example, paints, varnishes, lacquers, et but not including substances or wastes otherwise classified on account of their dangerous characteristic which give off a flammable vapour at temperatures of not more than 60.5°C, closed-cup test, or not more th 65.6°C, open-cup test. (Since the results of open-cup tests and of closed-cup tests are not strictly comparal and even individual results by the same test are often variable, regulations varying from the above figures make allowance for such differences would be within the spirit of this definition.)

- Flammable solid

Solids, or waste solids, other than those classed as explosives, which under conditions encountered transport are readily combustible, or may cause or contribute to fire through friction.

- Substances or wastes liable to spontaneous combustion

Substances or wastes which are liable to spontaneous heating under normal conditions encountered transport, or to heating up on contact with air, and being then liable to catch fire.

- Substances or wastes which, in contact with water emit flammable gases

Substances or wastes which, by interaction with water, are liable to become spontaneously flammable o give off flammable gases in dangerous quantities

- Oxidizing

Substances or wastes which, while in themselves not necessarily combustible, may, generally by yiel oxygen cause, or contribute to, the combustion of other materials.

- Organic Peroxides

- የኦክሲጂን-የኦክሲጂን (O-O) እስስር ያላቸዉ ኦረጋኒክ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች ሙ… መቋቋም ስለማይችሉ በራሳቸዉ ሀይል ሙቀት ተፊ (ኤክሶተርሚክ) ፍር… (ዲኮምፖዚሺን)ሊፍጥሩ ይችላሉ
- መርዛማ (አጣዳፊ)
- በሚዋጡበት ወይንም በምጋት (ኢንሄልድ) ወይንም በቆዳ ንክኪ በሰዉ ልጅ ላይ ሞትን ወይ… ከፈተኛ ጉዳትን የሚያስከትሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ተላላፊ በሽታዎችን የሚያስከትሉ ቁሳቁሶች

  ጥቅን ሕዋሳት (ማይክሮኦርጋኒዝም) ወይንም የእነሱን መርዝ የያዙና በእንስሳትና በሰዉ ላይ በሽ… ያስከትላሉ ተብለዉ የሚጠረጠሩ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ብሉት (ዝገት)

  በኬሚካዊ አፀግብሮት (chemical action) አማካይነት በህብረህዋሳት ጋር በሚፈጠር ግንኙ… ከፍትኛ ጉዳትን ወይንም እዠት(leakage) በሚከሰትበት ጊዜ በሌሎች ቁሳቁሶች ወይንም በማጓ… ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይንም የሚያበላሹ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ከአየር ወይንም ከዉሃ ጋር ግንኙነት በሚፈጠርበት ጊዜ የመርዛማ ጋዞች ልቀት

  ከአየር ወይንም ከዉሃ ጋር ግንኙነት በሚፈጠርበት ጊዜ መርዛማ ጋዞችን በአደገኛ መጠን ሊፈ… የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- መርዛማ (አርፍዳዊ ወይንም ስር ሰደድ)

  በምጋት፤ወይንም በመብላት /መጠጣት ወይንም ቆዳ ዉስጥ በመዝለቅ አርፍዳዊ ወይንም ስር ሰ… ጉዳቶችን ነቀርሳን ጭምር ይሚያስከትሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- መርዛማ (በአካባቢ ላይ)

  በአካባቢ ላይ ከተለቀቁ በክምችትና/ወይንም በመርዛማነት በአፋጣኝ ወይንም አርፍዳዊ ጉዳቶ… የሚያስከትሉ ወይንም ሊያስከትሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች ወይንም ቆሻሻዎች
- ከተወገደ በኋላ በማናቸዉም መንገድ ሌላ ቁሳቁስ ለምሳሌ በኬሚካዊ እጥበት (leaching) ከ… የተጠቀሱትን በሀርይ መፍጠር የሚችል

## አባሪ III

## የአወጋገድ ክንዋኔዎች

ሀ. የሀብት ሪከቨሪ :ምልልስነት ፤ተወጋጅን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል (reclamation)) በቀጥታ መልሶ… ይመጠቀምን ወይንም ሌላ አማራጭ ጥቅም ላይ ማዋልን የማያስከትሉ ክንዋኔዎች

ክፍል ፩ ሁሉንም የሚተገበሩ የአወጋገድ ክንዋኔዎች ያጠቃልላል

- በመሬት ላይ ማከማቸት ( ለምሳሌ ለባሳአፈር (landfill)
- የመሬት እንክብካቤ ( ለምሳሌ የፈሳሽ ቆሻሻዎች ባዮ ኩሰት (biodegradation)

Organic substances or wastes which contain the bivalent-o-o-structure are thermally unstable substances which may undergo exothermic self-accelerating decomposition

- Poisonous (Acute)

Substances or wastes liable either to cause death or serious injury or to harm human health if swallowed or inhaled or by skin contact

- Infectious substances

Substances or wastes containing viable micro organisms or their toxins which are known or suspected to cause disease in animals or humans.

- Corrosives

Substances or wastes which, by chemical action, will cause severe damage when in contact with living tissue, or, in the case of leakage, will materially damage, or even destroy, other goods or the means of transport; they may also cause other hazards.

- Liberation of toxic gases in contact with air or water

Substances or wastes which, by interaction with air or water, are liable to give off toxic gases in dangerous quantities.

- Toxic (Delayed or chronic)

Substances or wastes, which if they are inhaled or ingested or if they penetrate the skin, may involve delayed or chronic effects, including carcinogenicity.

- Ecotoxic

Substances or wastes which if released present or may present immediate or delayed adverse impacts to the environment by means of bioaccumulation and/or toxic effects upon biotic systems.

- Capable, by any means, after disposal, of yielding another material, e.g., leachate, which possesses any of the characteristics listed above.

## ANNEX III

## DISPOSAL OPERATIONS

**A. Operations which do not lead to the possibility of resource recovery, recycling, reclamation, direct re-use or alternative uses**

Section A encompasses all such disposal operations which occur in practice.

- Deposit into or onto land, (e.g., landfill, etc.)
- Land treatment, (e.g., biodegradation of liquid or sludgy discards in soils, etc.)

- በጥልቀት ማስገባት (ለምሳሌ በአየር መነፋት የሚቻሉትን ቆሻሻዎች ወደ ጥልቅ ጉድጓዶች የሚገኙ የጨዉ እንቁላሎች (salt domes) ወዘተ. ማስገባት)

  በመሬት ላይ (ለምሳሌ ፈሳሽ ቆሻሻዎችን በጉድጓዶች፣ ኩሬዎች ወይንም ቆራጭ (lagoons) ወዘተ.)ማጠራቀም

- በተለይ የተሰራ ለባሳአፈር (landfill) (ለምሳሌ የሚከደኑና እያንዳንዳቸዉ ከሌላዉና ከአካባቢ የማይገናኙ "lined discrete cells" ወዘተ.)
- ከባህሮች/ዉቂያኖሶች በስተቀር ወደ ተጠራቀመ ዉሃ (water body) መልቀቅ
- ወደ ባህሮች/ዉቂያኖሶች የባህር ወለል ጭምር ማስገባት
- በዚህ አባሪ ያልተካተተ ሀይወታዊ (ባዮሎጂካል) ክንዉን ሆኖ በመጨረሻ የሚገኘዉ ዉህድ ድብልቅ በክፍል ፩ በተጠቀሱት ማናቸዉም የአወጋገድ ክንዋኔዎች የሚፈጸም
- በዚህ አባሪ ያልተካተተ ፊዚኮ-ኬሚካዊ ክንዉን ሆኖ በመጨረሻ የሚገኘዉ ዉህድ ወይንም በክፍል ፩ በተጠቀሱት ማናቸዉ ም የአወጋገድ ክንዋኔዎች የሚፈጸም (ለምሳሌ ትነት፣ ማደ (calcinations)፣ኒዉትራላይዜሽን፣እትለት (ፕርሲፒትሽን)፣ ወዘተ.)
- በመሬት ላይ ማቃጠል

ለ. የሀብት ሪከቨሪ :ምልልስነት ፣ተወጋጅን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል (reclamation) በቀጥታ መልሶ ይመጠ ወይንም ሌላ አማራጭ ጥቅም ላይ ማዋልን የሚያስከትሉ ክንዋኔዎች

ክፍል ፪ ሁሉንም በህግ የትደነገጉትን ወይንም አደገኛ ቆሻሻዎች ተብለዉ የሚገመቱትንና በ ያልተፈረጁትን ክንዋኔዎች ያጠቃልላል

- ለነዳጅነት የሚያገለግል (በቀጥታ ማቃጠልን ሳይጨምር) ወይንም ሌላ ሀይል የማመንጫ መ
- አሟሚን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል/እቀጣይነት (regeneration)
- ለአሟሚነት ጥቅም ላይ የማይዉሉ ኦርጋኒክ ቁሳቁሶች
- ብረታብረቶችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል/እቀጣይነት(regeneration)
- ሌሎች ኢንኦረጋኒክ የሆኑ ቁሳቁሶችን ጥቅም ላይ ማዋል/እቀጣይነት(regeneration)
- አሲዶችንና ቤዞችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

- Deep injection, (e.g., injection of pumpable discards into wells, salt domes of naturally occurrin repositories, etc.)
- Surface impoundment, (e.g., placement of liquid or sludge discards into pits, ponds or lagoons,
- Specially engineered landfill, (e.g., placement into lined discrete cells which are capped and iso from one another and the environment, etc.)
- Release into a water body except seas/oceans
- Release into seas/oceans including sea-bed insertion
- Biological treatment not specified elsewhere in this Annex which results in final compounds or which are discarded by means of any of the operations in Section A
- Physico chemical treatment not specified elsewhere in this Annex which results in final compou mixtures which are discarded by means of any of the operations in Section A, (e.g., evaporatior calcination, neutralization, precipitation, etc.)
- Incineration on land

**B. Operations which may lead to resource recovery, recycling reclamation, direct re-use or alter uses**

Section B encompasses all such operations with respect to materials legally defined as or consi to be hazardous wastes and which otherwise would have been destined for operations inclu Section A

- Use as a fuel (other than in direct incineration) or other means to generate energy
- Solvent reclamation/regeneration
- Recycling/reclamation of organic substances which are not used as solvents
- Recycling/reclamation of metals and metal compounds
- Recycling/reclamation of other inorganic materials
- Regeneration of acids or bases
- Recovery of components used for pollution abatement